**ማስጠንቀቅያ/ የቤንዚን ባቡር**

**እውነታዎች:** ቤንዚን የጫነ ባቡር ከሃዲዱ የመልቀቅ ኣደጋ ሲያጋጥም፡ የኣደጋው ዓይነት እጅግ ኣስከፊ ነው ምክንያቱም ፍንዳታ፡ የቤንዚን መፍሰስ እንዲሁም የሌሎች ተጨማሪ ኬሚካሎች በኣካባቢው የመሰራጨት ኣደጋ ሊያስከትል ይችላልና። ይህም በመሆኑ በኣሁኑ ግዜ በሲያትል ኣካባቢ የህዝቡን ደህንነት ለመጠበቅ ከቤት ኣትውጡ ወይም ቤታችሁን ልቀቁ የሚል ትእዛዝ ኣስከትሎ ሊሆን ይችላል። ።

**ምን መደረግ ኣለበት**:

- የኣደጋ ተከላካዮች የሚሰጥዋቸውን መመርያዎች ሁሉ በደንብ ተከተሉ። ያሉበትን ቦታ ግምት ውስጥ በማስገባት ቤትዎን ለቀው እንዲወጡ ወይም ከቤትዎ እንዳይወጡ ሊጠየቁ ይችላሉ። ቤትዎን እንዲለቁ ሲታዘዙ በፍጥነት ውጡ።
- ሌሎች የኣደጋ ተከላካዮች በሚሰሩት ስራ ጣልቃ ኣትግቡ።
- ቤትዎን እንዳይለቁ ከታዘዙ ቤተሰቦንና ለማዳ እንስሳዎችዎን ቤት ውስጥ ኣስገቡ። በሮችን፡ መስኮቶችን እንዲሁም የጭስ ማውጫ በሮችን መዝጋት። ንፋስ ከውጭ ሊገባ በሚችልባቸው በየበሩና በየክፍተቱ ስር እርጥብ ፎጣዎችን ያስቀምጡ። በግድግዳ ላይ የተሰኩ የቀዝቃዛ ኣየርና የሙቀት መስጭያ መሳርያ ገመዶችን ንቀሉ። ከደጅ ምንም ዓይነት ንፋስ እንዳይገባ ለማገድና በእርስዎና በውጭ በሚገኘው ኣየር መካከል ምንም ዓይነት ግንኑነት እንዳይኖር ለማድረግ በኣጠገብዎ ያለውን ሁሉ ተጠቀሙ።
- ቤትዎን እንዲለቁ ሲታዘዙ፡ እባኮን ወድያውኑ ልቀቁ። በቤት መልቀቅ ማስጠንቀቅያ ላይ የተጻፉትን መንገዶች ተከተሉ'። ኣንዳንድ መንገዶች ምልክትና ማስጠንቀቅያ የተጻፈባቸው ሊሆኑ ይችላሉ።
- ኣደጋው ካጋጠመበት መንገድ ራቁ ።.
- ኣደጋውን በሚመለከት ኣዲስ መረጃ እንዳለ ለማወቅ በቀጣይነት ሬድዮ ተከታተሉ።

- ***ይህንን መልእክት ለመረዳት፡ ለማየትም ሆነ ለመሰማት የማይችል  የሚያውቁት ሰው ካለ፡ እባክዎትን መልእክትቱ ኣስረዱቸው።***

**ጠቃሚ ዌብሳይቶች:**

http://dot111.info/

http://www.fra.dot.gov/Page/P0001